### የ2025-2026 እና የ2026-2027 የትምህርት ዘመን የDCPS SELECTIVE ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ማመልከቻ ማሻሻያ

ከፍተኛ የልቀት ደረጃን እያስጠበቅን በዲስትሪክቱ ውስጥ ያሉ ሁሉም ተማሪዎች ለሚመረጡ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች/ፕሮግራሞች በእኩል ደረጃ ተደራሽ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ዲሲ የሕዝብ ትምህርት ቤቶች (DCPS) በየዓመቱ የተማሪ ቅበላ ፖሊሲዎቻች እና ሂደቶች ላይ ማሻሻያ የማድረግ እቅድ አለው። ዲስትሪክታችን ለእኩልነት እና ግልጽነት ባለው ትጋት መሰረት፣ DCPS በ25-26 እና 26-27 የትምህርት ዘመኖች ተፈጻሚ በሚደረጉት በሚመረጡ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት/ፕሮግራም የቅበላ መስፈርት እና ክፍሎች ላይ ያለውን መረጃ ሲያጋራ ደስታ ይሰማዋል። ለሁሉም የሚመረጡ የDCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት/ፕሮግራሞች በ www.myschooldc.org ያመልክቱ።

- **የPARCC/መደበኛ የፈተና ነጥብ መስፈርቶችን አለማካተት፥** DCPS የማሪዎች ቅበላ መስፈርት አንድ አካል በማድረግ እና ወደፊት ለሚኖሩ አስቀድመው ለታወቁ ጉዳዮች በድጋሚ PARCC ወይም የሌላ መደበኛ የፈተና ውጤቶችን አይሰበስብም ወይም አይቀበልም።
- **ውጤቶች እና ተሳትፎዎች፥** በዙርያው ላሉ ቤተሰቦች በሚፈለግ ሰነድ ዙርጣ ወጥነቱን የጠበቀ መረጃ ለመስጠት ሁሉም ትምህርት ቤቶች የቀድሞውን የትምህርት ዘመን የመጨረሻ የውጤት መግለጫ ካርድ እና የዚህን የትምህርት ዘመን የመጀመርያ የውጤት መግለጫ ካርድ ሁለቱንም ይቀበላሉ። በDCPS የውጤት አሰጣጥ ፖሊሲ መሰረት GPA እንዴት እንደሚሰላ ይገምግሙ።
- **ለቨርቿል ቅበላዎች ታሳቢ የሚደረጉ ጉዳዮች፡** በተሰጠ የጤና መመርያ እና የቤተሰብ ሁኔታ ላይ በመመስረት እንደ አስፈላጊነቱ እና ባለው ሁኔታ መሰረት ለ25-26 የትምህርት ዘመን የወሰኑ የምዝገባ ክፍሎች በቨርቿል ሊከናወኑ ይችላሉ። DCPS የጤና መመሪያን ለመቆጣጠር እና ለመከተል በቁርጠኝነት ይሰራል። በእያንዳንዱ ትምህርት ቤት የቨርቿ አገልግሎቶች ላይ ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት፣ እባክዎ የትምህርት ቤቶቹን የየራሳቸውን ድረገጾች ይመልከቱ።
- **የድጋፍ ደብዳቤዎች** የድጋፍ ደብዳቤ የሚሰጡ አካላት ማንነታቸው በይፋ የማይገለጽ መሆኑን እና የድጋፍ ደብዳቤዎች አንዴ ከገቡ በኋላ የመጨረሻ እና ለውጥ የማይደረግባቸው መሆኑን ልብ ይበሉ።

ከላይ ከተገለጹት ማሻሻያዎች በተጨማሪ፣ DCPS ተደራሽነታችንን በማስፋት እና የ8ኛ ክፍል ተማሪዎች የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ማመልከቻ ሲሞሉ ድጋፍ ከሚያደርጉላቸው የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር በመሳተፍ በየግል የትምህርት እቅዶች (IEPs) ለተማሪዎች ድጋፍ በሚያደርጉ መምህራን እና በየእንግሊዝኛ ቋንቋ ተማሪ (ELL) አገልግሎቶች ላይ በማትኮር ግልጽነትን እና እኩል ተደራሽነትን ማስፋፋቱን ለመቀጠልም ይተጋል።

እያንዳንዱ ትምህርት ቤት አስፈላጊ መስፈርቶችን እንዴት እንደሚገመግም ግልጽ መረጃ ለመስጠት ሁሉም ትምህርት ቤቶች በዚህ የበልግ ወቅት የብቃት መስፈርቶችን በድጋሚ ይለጥፋሉ። እነዚህ መስፈርቶች ለእያንዳንዱ መስፈርትምን ያህል ክብደት እንደሚሰጠው እና የተማሪውን ብቁነት እንዴት እንደሚወስኑ የሚገልጸውንም መረጃ የሚያካትቱ ሲሆን በDCPS የምዝገባ ድረ-ገጽ ላይ ይገኛሉ https://enrolldcps.dc.gov/node/201።

በተጨማሪም ወላጆች በአቅራቢያቸው ያሉ እጅግ በጣም ጥሩ የሆኑ ትምህርት ቤቶች ትኩረታቸው ልጆቻቸው ለኮሌጅ እና ለስራ ዝግጁ መሆናቸውን ማረጋገጥ መሆኑን እንዲያውቁ እንፈልጋለን። እያንዳንዱ የDCPS የስምንተኛ ክፍል ተማሪ በአቅራቢያው በሚገኝ ትምህርት ቤት ውስጥ በመላው ዲስትሪክቱ ውስጥ በሚገኙ የDCPS ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ሊገኝ የሚችለውን አካዳሚያዊ ፕሮግራም የሚገልጽ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ፣ የኮሌጅ እና የስራ ትምህርቶች (High School College and Career Academies) መመርያ ይሰጠዋል። መመርያው በአቅራቢያ የሚገኙ ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን እና የቅበላ ማመልከቻ የሚቀርብባቸውን (McKinley፣ Phelps እና CHEC) ጨምሮ የኮሌጅ እና የስራ ትምህርት የሚሰጥባቸውን የDCPS ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችን ያካትታሉ። በአካባቢ ወሰን ውስጥ ያለ ትምህርት ቤትዎን ያግኙ፥ https://enrolldcps.dc.gov/node/41።

| ትምህርት ቤቶች | የማመልከቻ ክፍሎች | | | | | | የቅበላ ሂደት (*በመጀመሪያ የኦንላይን ማመልከቻው ይገመገማል ከዚያም ትምህርት ቤቶች ከዚህ በታች ያሉትን ቀጣይ እርምጃዎች በተመለከተ ግንኙነት ያደርጋሉ*) ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ MySchoolDC.org የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | ሪፖርት ካርድ | | | ጽሁፍ | የድጋፍ ደብዳቤዎች (*በሚከተለው በኩል በኦንላይን የገባ My School DC ማመልከቻ*) | | |
| | የሚሸፈነው ጊዜ | GPA<br>የድጋፍ ደብዳቤ | የተሳትፎ መስፈርቶች | | # | ዓይነት | |
| **Bard High School Early College DC** | የ SY23-24 የመጨረሻ እና የ SY24-25 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያስፈልጋል[1] | 2.0 ወይም ከዛ በላይ የሆነ GPA ይመከራል | የለም | አዎ (*በአካል ተሰጥቷል*) | 2 | የእንግሊዝኛ አስተማሪ<br>የሂሳብ አስተማሪ | ግላዊ ቃለ መጠይቅ እና በአካል በሚገኝት የሚዘጋጅ ጽሁፍ |
| **Benjamin Banneker ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት** | የ SY23-24 የመጨረሻ እና የ SY24-25 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያስፈልጋል | የለም | የለም | አዎ<br>(*ኦንላይን በMSDC መተግበርያ የቀረበ እና በአካል በመገኘት የተሰጠ የጽሁፍ ዝግጅት ድጋፍ።*) | 3 | የእንግሊዝኛ አስተማሪ<br>የሂሳብ አስተማሪ<br>ካውንሰለር ወኡም አስተዳዳሪ | የቤተሰብ ቃለ መጠይቅ |
| **Columbia Heights የትምህርት ካምፓስ[2]** | የ SY23-24 የመጨረሻ እና የ SY24-25 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያስፈልጋል[3] | የለም | *አቴንዳንስ በሪፖርት ካርድ ላይ መገለጽ አለበት* | አይ[4] | 2 | የእንግሊዝኛ አስተማሪ<br>የሂሳብ አስተማሪ | የተማሪው የግል ቃለ መጠይቅ |
| **Duke Ellington የስነ ጥበባት ት/ቤት** | የ SY23-24 የመጨረሻ እና የ SY24-25 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያስፈልጋል | የለም | የለም | አዎ | 3 | የሂሳብ አስተማሪ<br>የስነ ጥበብ አስተማሪ (ወይም ሌላ)<br>ካውንሰለር ወኡም አስተዳዳሪ | ኦዲሽን/ምዘና[5]<br>የቤተሰብ ቃለ መጠይቅ |
| **ቅድመ ኮሌጅ Academy @ Coolidge** | የ SY23-24 የመጨረሻ እና የ SY24-25 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያስፈልጋል | 3.0 ወይም ከዛ በላይ የሆነ GPA ይመከራል | የለም | አዎ | 2 | የእንግሊዝኛ አስተማሪ<br>የሂሳብ አስተማሪ | የቤተሰብ ቃለ መጠይቅ |
| **McKinley Technology ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት** | የ SY23-24 የመጨረሻ እና የ SY24-25 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያስፈልጋል | 3.0 ወይም ከዛ በላይ የሆነ GPA ያስፈልጋል (እንግሊዘኛ፣ ታሪክ፣ ሂሳብ እና ሳይንስ) | የለም | አዎ (*በአካል ተሰጥቷል*) | 2 | የእንግሊዝኛ አስተማሪ<br>የሂሳብ አስተማሪ | የቡድን ቃለመጠይቅ እና በአካል በመገኘት የሚዘጋጅ ጽሁፍ |
| **የ Phelps አርክቴክቸር፣ ኮንስትራክሽን/ግንባታ እና ምህንድስና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት** | የ SY23-24 የመጨረሻ እና የ SY25-26 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያስፈልጋል | 2.5 ወይም ከዛ በላይ የሆነ GPA ይመከራል | *አቴንዳንስ በሪፖርት ካርድ ላይ መገለጽ አለበት።* | አዎ (*በአካል ተሰጥቷል*) | 2 | የሂሳብ አስተማሪ<br>ካውንሰለር ወኡም አስተዳዳሪ | ግላዊ ቃለ መጠይቅ እና በአካል በመገኘት የሚዘጋጅ ጽሁፍ |
| **የ School Without Walls ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት** | የ SY23-24 የመጨረሻ እና የ SY24-25 የመጀመሪያ ሩብ ዓመት ያስፈልጋል | 3.0 ወይም ከዛ በላይ የሆነ GPA ያስፈልጋል፤ 3.5 ወይም ከዛ በላይ የሆነ GPA ይመከራል | የለም | አዎ (*በአካል ተሰጥቷል*) | 2 | የእንግሊዝኛ አስተማሪ<br>የሂሳብ አስተማሪ | የቤተሰብ ቃለ-መጠይቅ እና በአካል በመገኘት የሚዘጋጅ ጽሁፍ |

[1] የ11ኛ ክፍል አመልካቾች ከውጤት መግለጫ ካርዳቸው በተጨማሪ ህጋዊ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትራንስክሪፕት ማቅረብ አለባቸው።
[2] የ8ኛ ክፍል ትምህርታቸውን CHEC ውስጥ ያጠናቀቁ ተማሪዎች ከMy School DC የእጣ ማመልከቻ ውጪ 9ኛ ክፍልን ለመማር CHEC ውስጥ የመመዝገብ መብት አላቸው።
[3] የ11ኛ እና 12ኛ ክፍል አመልካቾች ከውጤት መግለጫ ካርዳቸው በተጨማሪ ህጋዊ የከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትራንስክሪፕት ማቅረብ አለባቸው።
[4] የCHEC አመልካቾች በMy School DC መተግበርያ የሚሞላውን የተማሪ ፍላጎት የዳሰሳ ጥናት መሙላት አለባቸው።
[5] በDuke Ellington የስነ ጥበባት ት/ቤት የሚገኙ ሁለት ፕሮግራሞች ተጨማሪ መረጃ እንዲሰጥ ይፈልጋሉ። ለተጨማሪ መረጃ እባክዎ MySchoolDC.org የሚለውን ድረ ገጽ ይጎብኙ።